## ምዕራፍ ፴

### በደብረ ታቦር ምንባብ

፩ በስመ እግዚአብሔር ዘበሥላሴሁ
ዘይትዋሐድ፡ እምህላዌሁ ዘኢይትበዐድ፡ ዘኢይ
ትኔጸር በዓይን ወኢይትገሰስ በእድ፡ ዘሰቀሎ
ለሰማይ እንበለ ዓምድ፡ ወዘአጽንዓ ለምድር
ዘእንበለ ድድ፡ በከርሠ ደመና ክቡድ ማየ ርጉዐ
ዘይኤልድ እምፍተታቲሁ ጸዓድዒድ፡ ዘይዌጽፎ
ለአብራድ፡ ዘያጌጉኦ ለጊሜ ከመ ሩፀተ መራድ፡
ወይዘርዎ ከመ ሐመድ፡ ዘይነድኦሙ ለነጠብጣበ
ዝናማት ውስተ ፍና ኀበ ይትፌቀድ፡ በቃለ ፀዓዕ
ወነጐድጓድ፡ወበንጥረ መባርቅት መርዕድ፡ ዘይ
ፌጽም ልደተ ጥንተዮን ዘበሳብዕ ምዕዋድ፡ ወለአ
ናቅጸ አበቅቴሰ ዘያስተባርዮን እሙላድ ውስተ
ሙላድ፡ እስከ ፲ወ፱ ዘመድ፡ ወፍቅደ ሙላዶንሰ
ዘበበዐሥሩ ወአሐቲ እንዘ ይፌደፍድ፡ ወዘበበ
ዐሠሩ ወተሱዕ እንዘ ይወሕድ፡ እንዘ ኢየኀልቅ
ትልቄ ዓመታቲሆን ለትውልደ ትውልድ፡
አሜን።

፪ ንጽሐው እንከ እምድኅረ ሞተ
ብጻው ክቡድ ዘያንኮልሉ ለድማሕ ከመ ስቴ
ክርዳድ ዘውስተ እደ መያሲ፡ ከመ ናይድዕ ዘለፋ
ሆሙ ለክርዱዳነ ልብ ወክርዱዳነ ኅሊና፡ ወለክ
ርዱዳነ ንባብ፡ ወለክርዱዳነ ትምህርት እለ ይትክ
ሐዱ ትንሣኤ ምውታን በመትልወ ትምህር
ቶሙ ለሰዱቃውያን።

፫ እስመ ሰዱቃውያንሰ ፍሉጣን እሙንቱ
እምሕዝበ አይሁድ በእንተ ዘገብሩ ኑፋቄ በኢአ
ሚነ ትንሣኤ ምውታን።እስመ ጸሐፍትሰ ወፈሪ
ሳውያን ይትአመኑ በትንሣኤ ምውታን። ወባሕ
ቱ ሉቱፋነ ክሕደት ምስለ ሰዱቃውያን በእንተ
ልደቱ ለክርስቶስ እምድንግል።ወበእንተዝ ፈልፈ
ለ ጥበብ ጳውሎስ መከረ ያስተክሕዶሙ አመ
አቀምዎ ውስተ ዓውድ ከመ ይኲንንዎ በእንተ
ዘይሰብክ በስመ ኢየሱስ ክርስቶስ። ነጸረ ዐውደ
ከመ ገጸ ፩ ሰዱቃውያን ወገጸ ፩ ፈሪሳውያን ።
ከልሐ ወይቤ አንሰ ፈሪሳዊ ወልደ ፈሪሳዊ በእ
ንተ ተስፋ ሕይወተ ምውታን እትኬነን። ወሶበ
ከመዝ ይቤ ተበአሱ ፈሪሳውያን ወሰዱቃውያን።
ወተናፈቁ ኲሎሙ ሰዱቃውያን ወይቤሉ ኢየሐ
ይዉ ምውታን ወአልቦ መላእክት ወኢ መንፈስ
ቅዱስ። ወፈሪሳውያንሰ የአምኑ ከመ ቦ ዝንቱ
ኲሉ።ወኮነ ዐቢይ አውያት ወተንሥኡ ጸሐፍት

## ምዕራፍ ሠላሳ

### የደብረታቦር ምንባብ

፩ በሦስትነቱ አንድ በሆነ በባሕርዩ
በማይለይ በዓይን በማይታይ በእጅም በማይዳሰስ
ሰማይን ያለ ምሰሶ ባቆመ ምድርንም ያለ
መሠረት ባጸናት በከባድ ደመና ማኅፀን የረጋ
ውኃን በሚቋጥር ነጫጭ ከሆኑ አካላቱ በረዶን
የሚያስወነጭፍ እንደ ጠብጣቢ ሩጫም ጉምን
የሚያስኬደው እንደ ትቢያም የሚበትነው በብል
ጭታና በነጐ ድጓድ በሚያስፈራም የመብረቆች
ብልጭታ የዝናሞችንም ጠብታዎች ወደሚሻበት
በሚልካቸው በእግዚአብሔር ስም፡ በሰባተኛም
ዑደት የጥንትዮንን ልደት በሚፈጽም የአበቅቴን
ደጆች ግን ከመወለጃ እስከ መወለጃ እስከ አሥ
ራዘጠነኛው ዘመድ በሚያፈራርቃቸው የመወለጃ
ቸውም ቁጥር በየአሥራ አንድ እየተባዛ በየአሥ
ራ ዘጠኝም እየተቀነሰ የልጅ ልጆችም የዓመታት
ቁጥር አያልቅም ለዘላለሙ አሜን።

፪ እንግዲህ በጠላ ጠማቂ እጅ እንዳለ
እንደ እንክርዳድ ጠላ አናት የሚያሰክር ጽኑ
ቧልትን ከማውጋት ርቀን የሰዱቃውያንን ትምህ
ርት በተመለከተ የሙታንን መነሣት የካዱ ልባ
ቸው እንክርዳድ ኅሊናቸውም እንክርዳድ ንግግ
ራቸውና ትምህርታቸው እንክርዳድ የሆነ የእነ
ርሱን ተግሣጽ እንናገር ዘንድ እንትጋ።

፫ ሰዱቃውያንስ የሙታንን መነሣት ባለ
ማመን ባደረጉት ጥራጥሬ ከአይሁድ ወገኖች
የተለዩ ናቸው እኮን። ጻፎችና ፈሪሳ ውያን ግን
በሙታን መነሣት ያምናሉ ነገር ግን ክርስቶስ
ከድንግል መወለዱን በመካድ ከሰዱቃውያን ጋር
የተባበሩ ናቸው። ስለዚህም የጥበብ ምንጭ
ጳውሎስ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በማስተማሩ
ምክንያት በፍርድ አደባባይ ባቆሙት ጊዜ እርስ
በርስ ሊያሟግታቸው አሰበ። በሸንጐ ያሉት
እኩሌቶቹ ሰዱቃውያን እኩሌቶቹም ፈሪሳውያን
እንደሆኑ ተመለከተ። እኔ የፈሪሳዊ ልጅ ፈሪሳዊ
ነኝ ብሎ ጮኸ። እንዲህም ባለ ጊዜ ፈሪሳውያንና
ሰዱቃውያን እርስ በርሳቸው ተጣሉ
ሰዱቃውያንም ሁላቸው ተከፋፈሉ፡ ሙታን
አይነሡም መላእክትና የሉም መንፈስቅዱስም
የለም አሉ።ፈሪሳውያን ግን ይህ ሁሉ እንዳለ
ያምናሉ።ታላቅ ፍጅት ሆነ ጻፎችና ፈሪሳው

ወፈሪሳውያን ወተበአስዎሙ ወተላኰይዎሙ
ለሰዱቃውያን፡፡ ወይቤሉ አልቦ ዘረከብነ እኩየ
ላዕለ ዝ ብእሲ እንዳኢ ለእመሁ መንፈስቅዱስ
ተናገሮ ወእመ አኮ መልአክ፡፡ ወበዝ ምክር ድኅነ
ጳውሎስ እምኰነኔ እስመ አስተበአሶሙ ለእለ
ይትበአስዎ፡፡ ሐዋ ፳፫:፮-፲

፬ ወበወንጌልሂ ዜነወ ወንጌላዊ ዘከመ
መጽኡ ኀቤሁ ለእግዚእ ኢየሱስ ሰዱቃውያን እለ
ኢየአምኑ ትንሣኤ ምውታን፡፡ ወተስእልዎ ወይ
ቤልዎ ሊቅ ሙሴ ጸሐፈ ለነ እንዘ ይብል ለእ
መቦ ዘሞተ እትሁ ወኅደገ ብእሲቶ ወአልቦ
ውሉድ ያውስባ እትሁ ለብእሲቱ ወያቅም ዘርአ
ለእትሁ፡፡ወሀለዉ እንከ ኀቤነ ፯ አኃው፡፡ ወአው
ሰባ ዘይልህቅ ውእቱ ወአልቦ ውሉድ፡፡ ወከማሁ
አውሰባ ካልኡሂ ወሣልሱሂ ወኢኅደጉ ውሉደ፡፡
ሰብዓቲሆሙ ከማሁ አውሰብዋ ወሞቱ እንዘ
አልቦሙ ውሉድ፡፡ ወድኅረ ኵሎሙ ሞተት ይእ
ቲ ብእሲት፡፡አመ የሐይዉ እንከ ምውታን ለመ
ኑ ትከውኖ ብእሲቶ፡ እስመ ናሁ ሰብዓቲሆሙ
አውሰብዋ፡፡

፭ ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤ
ሎሙ ውሉደ ዝንቱ ዓለም ያወስቡ ወይትዋሰቡ
ይወልዱ ወይትዋለዱ፡፡ወእለሰ ይደልዎሙ
ይርከብዎ ለዝንቱ ዓለም አመ የሐይው ምው
ታን ኢያወስቡ ወኢይትዋሰቡ ወኢይመውቱ ዳግ
መ፡፡ አላ ይከውኑ ከመ መላእክተ እግዚአብሔር
እሙንቱ ወውሉደ ሕይወት እመንቱ፡፡ ማቴ
፳፪:፳፫-፴፫

፮ ወከመሰ የሐይዉ ምውታን ሙሴኒ
ነገረ ዘይቤሎ እግዚአብሔር በኀበ ዕፀ ጳጦስ አነ
ውእቱ አምላከ አብርሃም ወአምላከ ይስሐቅ
ወአምላከ ያዕቆብ፡፡ ኢኮነኬ አምላከ ምውታን አላ
አምላከ ሕያዋን ውእቱ እስመ ኵሎሙ ሕያዋን
እሙንቱ በኀቤሁ፡፡ ዘጸ ፫:፮

፯ ስምዑኬ ኦ ለባውያን ዘከመ ገብረ
እግዚእነ ቅሥተ ምስለ ሰዱቃውያን በቃለ ኦሪት
ዘይቤ እግዚአብሔር አነ ውእቱ አምላከ
አብርሃም ወአምላከ ይስሐቅ ወአምላከ ያዕቆብ፡፡
ኢኮነኬ አምላከ ምውታን አላ አምላከ ሕያዋን፡፡
እስመ ሕያዋን እሙንቱ በኀቤሁ፡፡ ለአብርሃም
ወለይስሐቅ ወለያዕቆብ አእመርነ ጥዩቀ ዜና
ሞቶሙ በመጽሐፈ ሕግ እንተ ምልእት ስብሐተ
እግዚአብሔር ዘኢይትሔሰው ቃሉ፡፡ ወዘይቤሰ
ወልደ እግዚአብሔር እስመ ከመ ሕያዋን እሙ
ንቱ በኀቤሁ አማንኬ ሕያዋን አብድንት በኀበ
ዘአውፅአ ነፍሶሙ እምሥጋሆሙ፡፡እስመ የአም
ር መሣጢሃ ለነፍስ ከመ ይሠውጣ ካዕበ ውስተ
ማኅፈደ ሥጋሃ፡፡

ያንም ተነሥተው ተጣሉ አቸው ሰዱቃውያ
ንንም ተተነኳኰሏቸው፡ በዚህ ሰው ላይ ያገኘነው
ክፉ ነገር የለም እንጃ መንፈስቅዱስ ወይም
መልአክ ተናግሮት ይሆን አሉ፡፡ በዚህ ምክር
ጳውሎስ ከፍርድ ዳነ የሚጣሉትን እርስ በርሳ
ቸው አጣልቷቸዋልና፡፡ሐዋ ፳፫:፮-፲

፬ በወንጌልም ወንጌላዊው የሙታንን
መነሣት የማያምኑ ሰዱቃውያን ወደ ጌታ
ኢየሱስ እንደመጡ ተናግሯል እንዲህም ብለው
ጠየቁት መምህር ሆይ ሙሴ ወንድሙ ልጆች
ሳይኖሩት ሚስቱን ትቶ የሞተበት ካለ ወንድሙ
ሚስቱን ያግባት ለወንድሙም ዘር ያቁምለት
ብሎ ጻፈልን እንግዲህ በእኛ ዘንድ ሰባት ወንድ
ማማቾች ነበሩ ታላቃቸው አገባት ሞተ ልጆ
ችም አልነበሩትም፡ሁለተኛውም ሦስተኛውም
እንደርሱ እያገቡአት ሞቱ ልጆችም አልተዉም
ሰባቱም እንደርሱ አገቧት ልጆች ሳይኖራቸውም
ሞቱ ከሁሉም በኋላ ያች ሴት ሞተች እንግዲህ
ሙታን በሚነሡ ጊዜ ለማንኛው ሚስት ትሆ
ናለች እነሆ ሰባቱ ሁሉ አግብተዋታልና ብለው
ጠየቁት፡፡

፭ ጌታ ኢየሱስም መልሶ አላቸው
የዚህ ዓለም ልጆች ያገባሉ ይጋባሉ ይወልዳሉ
ይዋለዳሉ፣ወዲያኛውን ዓለም ይወርሱአት ዘንድ
የተገባቸው ግን ሙታን በሚነሡ ጊዜ አያገቡም
አይጋቡም ዳግመኛም አይሞቱም እንደ እግዚ
አብሔር መላእክት ይሆናሉ የሕይወት ልጆችም
ናቸው እንጂ፡፡ ማቴ ፳፪:፳፫-፴፫

፮ ሙታን እንደሚነሡ ሙሴም
እግዚአብሔርም በጳጦስ ቁጥቋጦ አጠገብ እኔ
የአብርሃም አምላክ የይስሐቅ አምላክ የያዕቆ
ብም አምላክ ነኝ ያለውን ተናገረ የሕያዋን አምላ
ክ እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም ሁላቸው
በእርሱ ዘንድ ሕያዋን ናቸውና፡፡ ዘጸ ፫:፮

፯ ዐዋቆች ሆይ ጌታችን እግዚአብሔር
እኔ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅ አምላክ
የያዕቆብም አምላክ ነኝ በሚለው የኦሪት ቃል
ከሰዱቃውያን ጋር እንደተከራከረ ስሙ የሕያዋን
አምላክ እንጂ የመታን አምላክ አይደለም በእርሱ
ዘንድ ሕያዋን ናቸውና ቃሉ የማይታበል የእግዚ
አብሔርን ምስጋና በተመላች የሕግ መጽሐፍ
የአብርሃምና የይስሐቅን የያዕቆብንም የሞታ
ቸውን ዜና ፈጽመን ዐውቀናል የእግዚአብሔር
ልጅ በእርሱ ዘንድ ሕያዋን ናቸውና ያለው
በእውነት ነፍሳቸውን ከሥጋቸው ባወጣ ጊዜ
በእርሱ ዘንድ በድኖች ሕያዋን ናቸው ሁለተኛ
ወደ ሥጋዋ አዳራሽ ይጨምራት ዘንድ የነፍስን
ነጣቂዋን ያውቃልና፡፡

፰ በከመ ይቤ በእንተ ነፍሱ ብውሕ ሊተ አንሥኣ ወብውሕ ሊተ አንብራ።ወእመሰ ወካዕ በመ ብውሕ ሎቱ ሠዊጠ መንፈሱ ኀበ ሥጋሁ።እፎኬ ኢይከውኖሙ ሠዊጠ መንፈሶሙ ለአብ ድንት ኀበ ማኅፈደ ሥጋሆሙ። ወበእንተዝ ይቤ ጳውሎስ እመሰ ኢይትነሥኡ ምውታን ክርስቶስኒ ኢተንሥአ እምውታን። ወእመሰ ክርስቶስ ኢተንሥአ እምውታን ከንቱኬ ተስፋክሙ ወከንቱ ሃይማኖትክሙ። ወንሕነኒ ኮነ ሰማዕተ ሐሰት ወንቤ ተንሥአ ክርስቶስ እምውታን ዘኢተንሥአኑ። ዮሐ ፲:፲፰ ፩ቆሮ ፲፭:፲፪-፲፱

፰ ስለ ነፍሱ አነሣት ዘንድ ሥልጣን አለኝ ላኖራትም ሥልጣን አለኝ እንዳለ ነፍሱን ከሥጋው ለመውሰድ ሥልጣን ካለው ዳግመኛም ነፍሱን ወደ ሥጋው ለመመለስ ሥልጣን አለው ታዲያ እንዴት የሙታንን ነፍስ ወደ ሥጋቸው አዳራሽ መመለስ አይቻለውም። ስለዚህም ጳውሎስ ሙታን ካልተነሡ ክርስቶስም ከሙታን ተለይቶ አልተነሣም ክርስቶስም ከሙታን ካልተነሣ ተስፋችሁ ከንቱ ነው ሃይማኖታችሁም ከንቱ ነው እኛም የሐሰት ምስክሮች ሆንን ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ አልን፣ ያልተነሣውን ነውን አለ። ዮሐ ፲:፲፰ ፩ቆሮ ፲፭:፲፪-፲፱

፱ ወካዕበ ይቤ ጳውሎስ ሀሎኑ ዘይብል እፎኑ ይትነሥኡ ምውታን ወበአይ ነፍስቶሙ የሐይዉ።ኦ አብድ አንተ ዘትዘርእ ኢየሐዩ ለእመ ኢሞተ ወዘኒ ዘትዘርእ አኮኑ ዝንቱ ነፍስት ዘይትወለድ ዘትዘርእ ዳእሙ ሕጠተ እመኒ ዘሥርናይ ወእመኒ ዘባዕድ ወእግዚአብሔር ይሁ ቦ ነፍስተ ዘከመ ፈቀደ። አማንኬ ጽሩይ ወጽዱቅ ቃለ ትምህርቱ ለጳውሎስ፡ በከመ ኢይክል ሕጠተ ሰገም ዘተዘርአ ውስተ መሬተ ምድር ወመዊቶ አመ በቄለ ከመ ይትመየጥ ሰብሉ ኀበ ሰዊተ ሥርናይ። ከማሁ ኢይክሉ ኃጥአን እለ ሞቱ በሥጋሆሙ ወተቀብሩ ውስተ መሬተ ምድር ከመ ይኩኑ ጻድቃነ አመ ትንሣኤ ምውታን።

፱ ዳግመኛም ጳውሎስ ሙታን እንዴት ይነሣሉ በየትኛው ሰውነታችውም ይነሣሉ የሚል አለን አንተ ሰነፍ አንተ የምትዘራው ካል ሞተ አይነሣም አንተ የምትዘራው ቅንጣት የስንዴም ቢሆን ሌላም ቢሆን እግዚአብሔር እንደ ወደደ አካልን ይሰጠዋል አለ። በእውነት የጳውሎስ የትምህርቱ ቃል የጠራና እውነተኛ ነው በምድር አፈር ላይ የተዘራ የገብስ ቅንጣት በስብሶ በበቀለ ጊዜ ሰብሉ ወደ ስንዴ እሸትነት መለወጥ እንደማይችል እንዲሁ በሥጋቸው ሞተው በምድር አፈር ውስጥ የተቀበሩ ኃጥአን በሙታን መነሣት ጊዜ ጻድቃን ይሆኑ ዘንድ አይቻላቸውም።

፲ ወበከመ ኢይክል ካዕበ ኀጠተ ሥርናይ ዘተዘርአ ውስተ መሬተ ምድር ወመዊቶ አመ በቈለ ከመ ያውጽእ ሕጠተ ሰገም ውስተ መስበልቱ። ወከማሁ ኢይክል ብእሲ ጻድቅ ዘሞተ በሥጋሁ ከመ ይኩን ኃጥአ አመ ትንሣኤ ምውታን። ወበእንተዝ ይቤ ጳውሎስ ዘዘርአ በሥጋሁ የአርር ሕይወተ ዘለዓለም። ወካዕበ ይቤ ይዘራእ በዘይማስን ወይትነሣእ በዘኢይማስን፡ይዘራእ በኃሣር ወይትነሣእ በክብር። ይዘራእ በድካም ወይትነሣእ በኃይል፡ይዘራእ በሥጋ ዘነፍስ ወይትነሣእ በሥጋ ዘመንፈስቅዱስ። እመሰኬ ቦ ሥጋ ዘነፍስ ቦኬ ሥጋ ዘመንፈስ ። በከመ ክርስቶስ ተዐገሠ ኀፍረተ መስቀል ወሞተ በኃሣር ወተዘርአ ውስተ ልበ ምድር ከመ አብድንት ርኩሳን እንዘ ኢኮነ ርኩሰ በሥጋ እስመ ቅድሳተ መለኮት ሀሎ ምስሌሁ። ወአመ ሦጣ ለነፍሱ ውስተ ሥጋሁ ተንሥአ በክብር ወበስብሐት እስመ አልቦ ሥልጣን ሞት ላዕሌሁ። ፩ቆሮ ፲፭: ፴፭-፶፰

፲ ዳግመኛም በምድር አፈር ውስጥ የተዘራ የስንዴ ቅንጣት በስብሶ በበቀለ ጊዜ በአገዳው ላይ የገብስ ቅንጣት ያወጣ ዘንድ እንደማይችል እንዲሁ በሥጋው የዘራ የዘላለም ሕይወትን ያገኛል አለ። ዳግመኛም በሚጠፋ ገንዘብ ይዘራል በማይጠፋም ገንዘብ ይነሣል በኀሣር ይዘራል በክብርም ይነሣል በድካም ይዘራል በኃይልም ይነሣል ነፍስ ባለችው በሥጋ ይዘራል መንፈስቅዱስ በተዋሀደው ሥጋ ይነሣል። ነፍስ ያለችው ሥጋ ካለ መንፈስ የሚዋሐደው ሥጋ አለ። ክርስቶስ የመስቀል እፍረትን እንደታገሠ በኀሣር ሞተ በሥጋውም ርኩስ ሳይሆን እንደ ረከሱ በድኖች በምድር ልብ ውስጥ ተዘራ ቅዱስ መለኮት ከእርሱ ጋር አለና ነፍሱንም ወደ ሥጋ ው በመለሳት ጊዜ በክብርና በምስጋና ተነሣ ሞት በእርሱ ላይ ሥልጣን የለውምና ። ፩ቆሮ ፲፭: ፴፭-፶፰

፲፩ ወበእንተዝ ይቤ ጳውሎስ በከመ በእንተ አዳም ኵልነ ንመውት፡ ወከማሁ በእንተ ክርስቶስ ኵልነ ነሐዩ።ወተዘርኡ ሰማዕታት በኃሣር ውስተ ገጸ ምድር እስመ እምድኅረ ቀተልዎሙ በሥቃይ መምለክያነ ጣዖት ገደፍዎሙ

፲፩ ስለዚህም ጳውሎስ በአዳም ሁላችን እንደምንሞት እንዲሁ በክርስቶስ ሁላችን እንድናለን አለ። ሰማዕታት በምድር ላይ በመከራ ተዘሩ ጣዖት አምላኪዎች በሥቃይ ከገደሉአቸው በኋላ እንደውሾች በድን የአሕዛብ ነገሥታት በተከማቹበት ጥለዋ ቸዋልና።ነቢይ የአገልጋ

ከመ አብድንተ ከለባት ውስተ ኵርጓኔሆሙ ለነገሥተ አረሚ፡ በከመ ይቤ ነቢይ ወረሰዩ አብድንቲሆሙ ለአግብርቲከ መብልዐ ለአዕዋፈ ሰማይ፡ወሥጋሆሙኒ ለጻድቃኒከ ለአራዊተ ገዳም ::ወአመ ትንሣኤ ምውታን ይትነሥኡ በክብር ወበስብሐት በከመ ክርስቶስ ተንሥአ:: ወበእንተዝ ይቤ ጳውሎስ እምከመሰ ተሳተፍናሁ ለመርዓዊ በሞቱ ንትሜሰሎ በሕይወቱ::ወእምከመሂ ዐረይነ ሕማመ ንዔሪ ነጊሠ:: ወበእንተዝ ተፈጸመ ዘይቤ ይዘራእ በኀሣር ወይትነሣእ በክብር :: ሮሜ፰:፲፯ ፩ቆሮ ፲፭: ፵፫

ዮችህን በድኖቻቸውን ለሰማይ ወፎች መብል አደረጉ የጻድቃንህንም ሥጋቸውን ለምድረበዳ አውሬዎች ሰጡ እንዳለ::በሙታን መነሣት ጊዜ ግን ክርስቶስ በክብርና በምስጋና እንደተነሣ እነርሱም በፍጹም ክብር ይነሣሉ:: ስለዚህም ጳውሎስ ሙሽራውን በሞቱ ከተሳተፍነው በሕይወቱ እንመስ ለዋለን መከራን በመቀበልም ከተካከልን በመንግሥም እንተካከላለን እንዳለ :በዚህ ምክን ያት በኀሣር ይዘራል በክብርም ይነሣል ያለው ተፈጸመ :: ሮሜ፰:፲፯ ፩ቆሮ ፲፭: ፵፫

፲፪ ተዘርኡ ፈላስያን እለ ጕዩ እምትፍሥሕተ ዝንቱ ዓለም ተነጽሐ ውስተ ገጸ ገዳም እምአብዝኆ ጻማ እንዘ ይመጽሉ ሥጋሆሙ ከመ ሐምለ መሎኬ ዘመዋዕለ ዓባር እንዘ ይዴምን ገጸሙ ከመ ጸለሎ መቅጹት :: ወአመ ትንሣኤ ምውታን ይበርህ ገጸሙ ምስብዒተ እምፀሐይ:: ወይጸድል እምሥርቀተ ቤዝ ዘያንበለብል በገጸ ሰማይ:: ማቴ ፲፫:፵፫

፲፪ ከዚህ ዓለም ደስታ የተለዩ መናንያን ተበታተኑ ትሩፋት ከማብዛት የተነሣ በውርጭ ወራት እንደበቀለ ቅጠል ሥጋቸው ጠውልጎ ፊታቸውም እንደ ማሰሮ ጥላሸት ጠቁሮ በምድ ረ በዳ ወደቁ:: በሙታን መነሣት ጊዜ ግን ፊታ ቸው ከፀሐይ ሰባት እጅ ይበራል ክብራቸውም በሰማይ ጠፈር እንደሚያብረቀርቅ እንደ ኮከብ መውጣት ያበራል:: ማቴ ፲፫:፵፫

፲፫ ወለኃጥአንሰ አኮ ከማሁ:: እስመ ምግባሮሙ ታረስሖሙ ወኃጢአቶሙ ትዛለፎሙ::ወዘአስተሐቶሙ ይቀድም አተዋድዮቶሙ::ወበእንተዝ ይቤ ጳውሎስ ኵልነ ንመውት ወአኮ ኵልነ ዘንትዌለጥ ለእንተ ምዕር ለሰዓት ከመ ቅጽበተ ዓይን በደኃሪ ንፍሐተ ቀርን ወይነፍሑ ቀርነ ወይትነሥኡ ምውታን:: ወንሕነሰ ንትዌለጥ:: ናሁኬ ዜነወ ሐዋርያ ተወልጦ ጻድቃን እምኃሣረ ሞቶሙ ኀበ ትንሣኤ በክብር ወበስብሐት::ወለኃጥአንሰ ዕለተ ደይን ትጸንሖሙ::ይኄይስ ጻድቅ ዘኢይትአመር ተዝካረ ሞቱ እምኃጥእ ዘይገብሩ ሎቱ ተዝካረ በውሂበ ምጽዋት ወአጽገቦ ርኁባን ወበአርውዮ ጽሙአን፡ በከመ ይቤሉ ሐዋርያት ወለረሲዓንሰ ብዕለ ኵሉ ዓለም እምተውህበ ሎሙ አልቦ ዘይበቊዕ ፡፡ ወሶበ እንዘ በሕይወቱ ውእቱ ፀሩ ለእግዚአብሔር እፎኬ ተዐረኮ እምድኅረ ሞቱ፡ እስመ ኵሉ ዘያንሶሱ በጽልመት ያቀድም ማኅቶተ ቅድመ አዕይንቲሁ ከመ ያስተርኢ ሎቱ ፍኖት በብርሃነ ማኅቶት :: ወከማሁ ዘያቀድም ውሂበ ምጽዋት እንዘ ሀሎ በሕይወቱ ይትኃዋህ ሎቱ ጽልመተ ኃጣውኢሁ በብርሃነ ማኅቶት ዘውሂበ ምጽዋት::

፲፫ የኃጢአተኞች ግን እንዲህ አይደለም ሥራቸው ታስድፋቸዋለችና ኃጢአታቸውም ትዘ ልፋቸዋለችና ያሳታቸውም እነርሱን ለመክሰስ ይቀድማል:: ስለዚህ ጳውሎስ ሁላችን የምናን ቀላፋ አይደለንም ነገር ግን የኋለኛው መለከት ሲነፋ ሁላችን በድንገት በቅጽበተ ዓይን እንለወ ጣለን፡ መለከት ይነፋል ሙታንም ይነሣሉ አለ:: እነሆ ሐዋርያው የጻድቃንን ከሞታቸው ኀሣር ወደ ትንሣኤ ፍጹም ክብር መለወጥ ተናገረ ኃጥአንን ግን የፍርድ ቀን ትቆያቸዋለች:: የሞቱ መታሰቢያ የማይታወቅ ጻድቅ ምጽዋት በመስጠትና የተራቡትን ምቋጥ ገብ የተጠሙትንም በማርካት መታሰቢያ ከሚ ያደርጉለት ኃጢአተኛ ይሻላል:: ሐዋርያት ዝንጉዎች ግን የዓለምን ሁሉ ሀብት ቢሰጡ ላቸው የሚረባቸው የለም እንዳሉ በሕይወቱ ሳለ ለእግዚአብሔር ጠላት ከነበረ ከሞቱ በኋላ እንደምን ወዳጅ ይሆናል:: በጨለማ የሚጓዝ ሁሉ መንገዱ በመብራቱ ብርሃን እንዲታየው በፊቱ መብራት ያስቀድማል:እንዲሁም በሕይ ወቱ ሳለ ምጽዋት መስጠትን ያስቀደመ በመመ ጽወት መብራት ብርሃን ምክንያት የኃጢ አቶቹ ጨለማ ተገፎ ብርሃን ይሆለታል::

፲፬ ወካዕበ ለእመ አኀተው ሎቱ ፻፻ መኃትወ ድኅሬሁ ለዘነገደ ቅድመ ኢይበቁዖ ብርሃነ መኃትው፡ እስመ ጽላሎተ ርእሱ ያንሶሱ ቅድሜሁ ከመ ታዕቅፎ:: ወከማሁ ለዘሂኢያ ቅደመ ውሂበ ምጽዋት በሕይወቱ ይቀድማሁ ኃጣውኢሁ ወብርሃነ መኃትው እለ ይትኬወላሁ ኢባቊዕ ለርእሱ::ወዘሰ አቅደመ ውሂበ ምጽዋት በሕይወቱ እምድኅረ ፀአተ ነፍሱ እመ ተገብረ

፲፬ ዳግመኛም ቀድሞ ለሄደ ሰው ከኋላው አሥር ሺህ መብራት ቢያበሩለት የመብ ራቶቹ ብርሃን አይጠቅመውም::የገዛ ጥላው ልታ ደናቅፈው በፊቱ ትሄዳለችና ::እንዲሁም በሕይ ወቱ ምጽዋት መስጠትን ያላስቀደመ ኃጢአቶቹ ይቀድሙታል:ከኋላው የሚከተሉትም መብራ ቶች ብርሃን ለርሱ የሚጠቅም አይሆንም፡ በሕይ ወቱ ምጽዋት መስጠትን ያስቀደመ ግን ከነፍ

ተዝካረ ሞቱ በውሂበ ምጽዋት ይመስል መርዓዌ ሥርገወ ዘየዐውድዎ ብርሃነ መኃትው እስከ አመ ይበውእ ውስተ ቤተ መርዓ።

፲፭ ወበእንተሰ ትንሣኤ ምውታን ከመ ኢትትካሐዱ ይቤ ሕዝቅኤል ወኮነ ላዕሌየ እደ እግዚአብሔር ወአውፅአኒ መንፈሰ እግዚአብሔር ወአንበረኒ ማእከለ ገዳም ወምሉእ ህየ አዕጽምተ ሰብእ።ወአዖደኒ ውስቴቱ ወብዙኅ ፈድፋደ ውስተ ገጸ ገዳም ወይቡስ ጥቀ። ወይቤለኒ ወልደ እጓለ እመሕያው የሐይዉኑ ዝ አዕጽምት። ወእቤ እግዚኦ እግዚኦ አንተ ተአምር። ወይቤለኒ ተነበይ ለዝ አዕጽምት ወበሎሙ አዕጽምት ይቡስ ስምዑ ቃለ እግዚአብሔር ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር እግዚእ ለዝ አዕጽምት ናሁ አነ አመጽእ መንፈሰ ሕይወት ላዕሌክሙ ወእሁብክሙ ሥርወ ወአለብሰክሙ ሥጋ ወእሰፍሕ ላዕሌክሙ ማእሰ። ወእወዲ ውስቴትክሙ መንፈስየ ወተሐይዉ ወተአምሩ ከመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር። ወተነበይኩ በከመ አዘዘኒ።

፲፮ ወመጽአ ቃል ሶበ ተነበይኩ። ወናሁ ድልቅልቅ ወአስተጋብኦሙ ለአዕጽምት ውስተ መስያልዩ በበዚአሁ። ወነጸርኩ ወርኢኩ ሥርወ ላዕሌሆሙ ወበቈለ ሥጋሆሙ ወዐርገ ማእሰ ዲቤሆሙ ወአልቦሙ መንፈስ። ወይቤለኒ ወልደ እጓለ እመሕያው ተነበይ ወበላ ለመንፈስ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር እምአርባዕቱ ነፋሳት ትመጽእ ወትነፍሕ ላዕለ ዝንቱ አብድንት ወተሐዩ ።ወተነበይኩ በከመ አዘዘኒ ወቦአ ላዕሌ ሆሙ መንፈስ ወሐይዉ ወቆሙ በእገሪሆሙ ብዙኅ ሠራዊት ጥቀ።

፲፯ ወእግዚእነሂ ይቤ በወንጌል እስመ ወልደእግዚአብሔር ወልደ እጓለ እመሕያው ውእቱ ወበእንተ ዝንቱሰ ኢታንክሩ እስመ ይበጽሕ ጊዜሁ አመ ይሰምዕዎ ቃሎ ይሰምዕዎ ቃሎ መቃብር። ይወፅኡ እለሠናየ ገብሩ ውስተ ኵሎሙ እለ ውስተ ትንሣኤ ሕይወት ወእለሰ እኩየ ገብሩ ውስተ ትንሣኤ ዘለደይን። ዮሐ ፭:፳፱

፲፰ የአክል እንከሰ ስምዐ መጻሕፍት እለ ይነግራ በእንተ ትንሣኤ ምውታን። ለእመሰ በእሉንቱ ኅዳጣን ቃላተ መለኮት ኢአምኑ ወለእመ አብዛኅነ እምዝኒ ኢየአምኑ። ለዘሰ ድንቅው ውእቱ ቃለ ቀርን ኢይበውእ ውስተ እዘኒሁ። ወለዘሂ ዕውር ብርሃነ ፀሐይ ኢያስተርኢ ሎቱ ።ለዘሂ አብድ እበዲሁ ጥበበ ይመስሎ። ወነገረ ጠቢባንሰ ይገድፎ ከመ እዳዋት። ለእመ ኀጸብካ ለመሬተ ምድር በማይ ትዌስክ ፅቡረ በዲበ ፅቡር ወኢትክል አንጽሖታ። ወለእመ ገሠጽኮ

ሱም መውጣት በኋላ ምጽዋት በመስጠት የሞቱ መታሰቢያ ቢደረግ ወደ ሠርጉ ቤት እስኪገባ ድረስ በመብራቶች ብርሃን የሚያጅቡትን ያጌጠ ሙሽራን ይመስላል።

፲፭ ስለሙታን መነሣትም እንዳት ከራከሩ ሕዝቅኤል እንዲህ አለ፡በእኔም ላይ የእግዚአብሔር እጅ ነበረ የእግዚአብሔርም መንፈስ አወጣኝ በምድረ በዳም አኖረኝ፡ሥፍራውም በሰዎች አጥንት ተሞልቷል። በምድረ በዳ ውስጥ አብዝቶ አተዞረኝ ፈጽሞ ደረቅም ነበር አለኝም የሰው ልጅ ሆይ ይህ አጥንት ይድናልን አለኝ እኔም አቤቱ አንተ ታውቃለህ አልሁ። ለዚህ አጥንት ትንቢት ተናገር እናንተ የደረቃችሁ አጥንቶች የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ለእነ ዚህ አጥንቶች እነሆ እኔ በላያችሁ የሕይወትን መንፈስ አመጣለሁ ሥርን እሰጣችኋለሁ ሥጋን አለብሳችሁ በላያችሁም ቁርበት አደርጋለሁ በውሳጣችሁም መንፈሴን አኖራለሁ ትድኑማላችሁ እኔም እግዚአብሔር እንደሆንሁ ታውቃላችሁ በላቸው አለኝ ። እንዳዘዘኝም ትንቢት ተናገርሁ።

፲፮ ትንቢት በተናገርሁም ጊዜ ቃል መጣ መነዋወጥም ሆነ አጥንቶችንም በየመለያያው ለየራሳቸው ሰብሰባቸው ሥርን በላያቸው ተመለከትሁ ሥጋቸውም በቀለ ቁርበትም በላያቸው ወጣ መንፈስ ግን አልነበራቸውም። የሰው ልጅ ሆይ ትንቢት ተናገር መንፈስንም እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ከአራቱ ነፋሳት ትመጣለች እነዚህም በድኖች ላይ ትነፍሳለች ይድኑማል በላት አለኝ። እኔም እንዳዘዘኝ ትንቢት ተናገርሁ መንፈስም በእነርሱም ላይ ገቡ ድነውም በእግሮቻቸው ቆሙ እጅግ ብዙ ሠራዊትም ሆኑ።

፲፯ ጌታችንም በወንጌል የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅ ነውና ስለዚህም ነገር አታድንቁ በመቃብር ያሉት ሁሉ ቃሉን የሚሰሙበት ጊዜ ይመጣል፡ በጎ ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይነሣሉ አለ። ዮሐ ፭:፳፱

፲፰ እንግዲህስ ስለሙታን መነሣት የሚናገሩ የመጻሕፍት ምስክርነት ይበቃናል። በእነዚህ ጥቂት የመለኮት ቃሎች ካላመኑ ከዚህ የበዛም ብንናገር አያምኑም መስማት ለተሣነው ሰው የመለኮት ድምፅ በጆሮዎቹ አይገባም ማየት የተሳነውም የፀሐይ ብርሃን አይታየውም ሰነፍም ስንፍናው ጥበብ ይመስለዋል የጥበበኞችንም ነገር እንደ ጥራጊ ይጥለዋል። የምድርን አፈር በውኃ ብታጥባት በጭቃ ላይ ጭቃን ትጨምራለህ ማንጻትም አትችልም ሰነፍንም

ለአብድ በቃለ ጥበብ ይዌስክ እበደ በዲበ እበዲሁ ወኢትክል አጥብቦቶ፡፡

በጥበብ ቃል ብትገሥጸው በስንፍናው ላይ ስንፍናን ይጨምራል ዐዋቂም ልታደርገው አይቻልህም፡፡

፲፱ ወእምይእዜሰ ንግባእ ኀበ ዜና ነገር ዘወንጌላውያን ዘከመ አይድዑ በእንተ ዕርገተ ደብረ ታቦር፡፡ ማቴዎስኒ ይቤ እምድኅረ ስሱ መዋዕል ነሥኦሙ ለጴጥሮስ ወለዮሐንስ ወለያዕቆብ ወአዕረጎሙ ዲበ ደብር ነዋኅ ጥቀ እንተ ባሕቲቶሙ ወተወለጠ ርእየተ ገጹ በቅድሜሆሙ ወአልባሲሁኒ ኮነ ጸዓዳ ከመ ብርሃነ መብረቅ፡ወአስተርአይዎሙ ሙሴ ወኤልያስ እንዘ ይትናገሩ ምስሌሁ፡፡ ማቴ፲፯፡፩-፭

፲፱ እንግዲህስ ወደ ታቦር ተራራ ስለመውጣት ወደተናገሩ ወደ ወንጌላውያን ዜና ነገር እንመለስ፡፡ ማቴዎስ እንዲህ አለ፡ ከስድስት ቀን በኋላ ጴጥሮስንና ዮሐንስን ያዕቆብንም ይዟቸው ብቻቸውን ወደ ረጅም ተራራ አወጣቸው መልኩም በፊታቸው ተለወጠ ልብሱም እንደ መብረቅ ብርሃን ነጭ ሆነ ሆነ ሙሴና ኤልያስም ከእርሱ ጋር ሲናጋገሩ ታዩአቸው፡፡ማቴ፲፯፡፩-፭

፳ ወማርቆስኒ ይቤ ወአመ ሰዱስ ዕለት ነሥኦሙ እግዚእ ኢየሱስ ለጴጥሮስ ወለያዕቆብ ወለዮሐንስ ወአዕረጎሙ ደብረ ነዋኅ በባሕቲቶሙ ወተወለጠ ርእየተ ገጹ በቅድሜሆሙ ወአልባሲሁኒ በረቀ ከመመብረቅ ወጻዕደወ ከመ በረድ ዘኢይክል መሀፒል ከማሁ አጻዕድዎቶ በዲበ ምድር፡ ወአስተርአይዎሙ ሙሴ ወኤልያስ እንዘ ይትናገሩ ምሌሁ ለእግዚእ ኢየሱስ ፡፡

፳ ማርቆስ በስድስተኛውም ቀን ጌታ ኢየሱስ ጴጥሮስንና ያዕቆብን ዮሐንስንም ወሰዳቸው ብቻቸውንም ወደረጅም ተራራ አወጣቸው፡መልኩም በፊታቸው ተለወጠ ልብሱም እንደ መብረቅ አብለጨለጨ በምድር ላይ ሳሙና እንደዚያ አድርጎ ማንጻት እንደማይቻለው እንደ በረዶ ነጭ ሆነ፡ሙሴና ኤልያስም ከጌታ ኢየሱስ ጋር ሲነጋገሩ ታዩአቸው አለ፡፡ማር ፱፡፪-፭

፳፩ ሉቃስኒ ይቤ ወእምድኅረዝ ነገር በሳምንት ዕለት ነሥኦሙ እግዚእ ኢየሱስ ለጴጥሮስ ወለያዕቆብ ወለዮሐንስ ወዐርገ ደብረ ይጸሊ፡፡ ወእንዘ ይጼሊ ተወለጠ ርእየተ ገጹ ወአልባሲሁኒ ጻዕደወ ከመ መብረቅ፡፡ ወናሁ መጽኡ ፪ ዕደው ወይትናገሩ ምስሌሁ እሉ እሙንቱ ሙሴ ወኤልያስ እለ አስተርአዩ በስብሐቲሁ ዘሀሎ ይኩን በኢየሩሳሌም፡፡ ሉቃ ፱፡፩-፭

፳፩ ሉቃስም ከዚህም ነገር በኋላ በስምንተኛው ቀን ጌታ ኢየሱስ ጴጥሮስንና ያዕቆብን ዮሐንስንም ይዟቸው ሊጸልይ ወደ ተራራ ወጣ፡ ሲጸልይም መልኩ ተለወጠ፡ልብሱም እንደመብረቅ ነጭ ሆነ፡ እነሆም ሁለት ሰዎች መጡ ከእነርሱም ጋር ተነጋገሩ እነርሱም በክብር ተገልጠው በኢየሩሳሌም ይሆን ዘንድ ያለውን ክብሩን የተናገሩ ሙሴና ኤልያስ ናቸው አለ፡፡ ሉቃ ፱፡፩-፭

፳፪ ማቴዎስ ወማርቆስ ኀበሩ ቃለ በብሂለ አመ ስሱ ምስለ ብሂለ አመ ሰዱስ ለጎበ ፩ ይተረጎም፡፡ ወብሂለ እምዝ አመ ሰሙን አርእየ ኀበ ካልእ ፍና፡፡ ዘከመ እፎ እንከ ሌለየ ሉቃስ ዜንዎ እምአኃዊሁ፡፡ንንግርኬ እስመ ማቴዎስ ወማርቆስ ዜነዉ በሠርቀ ወርኅ ዘዕብራውያን ወዘሮማውያን እስመ አመ ሰሙኑ ለወርኃ ነሐሴ በአተ አብ በአውራኃ ዕብራውያን ወበአተ አውግስጦስ በአውራኃ ሮሜ፡፡ ለእመ ገደፍኮን ፮ መዋዕለ ነሐሴ መንገለ ተሙዝ በአውራኃ ዕብራውያን መንገለ ኢዮልዮስ በአውራኃ ሮሜ ይተርፍ ለከ እም ፲ወ፫ ሰዱሰ ወዋዕለ ሠርቀ ዘዕብራይስጢ ወዘሮማይስጥ፡፡ እስመ ኅቡራነ ሠርቅ እሙንቱ ወባሕቱ ስመ አውራኂሆሙ በበጽዋዔሆሙ፡፡ወበእንተዝ ይቤሉ ክልኤ ወንጌላውያን ወአመ ሰዱስ ነሥኦሙ ወሉቃስሰ ይቤ ወእምድኅረ ዝንቱ ነገር በሳምንት ዕለት ነሥኦሙ፡፡ እስመ ሠለስቲሆሙ ወንጌላውያን ነገሩ ዘከመ አቅደመ ብሂለ እግዚእ እምቅድመ ዕርገቱ ወስተ ደብረታቦር፡፡አማን አማን

፳፪ ማቴዎስና ማርቆስ አንድ ቃል ተናጋሩ፡፡ በስድስተኛው ቀን ማለትም በአንድ በኩል በስድስተኛው ቀን ተብሎ ይተረጉማል ከዚህ በኋላ በስምንተኛው ቀን ማለትም ደግሞ ሌላ መንገድ አሳየ፡ እንግዲህ ሉቃስ በመናገር ከወንድሞቹ እንዴት ተለየ ትርጓሜውን እንናገር፡፡ ማቴዎስና ማርቆስ በዕብራውያንና በሮማውያን የወር መባቻ ተናገሩ ነሐሴ ስምንት ቀን በዕብራውያን ወሮች የአብ መግቢያ በሮሜም ወሮች የአውግስጦስ መግቢያ ነውና፡፡ ሰባቱን የነሐሴን ቀኖች ከተውኸው በዕብራውያን ወሮች ወደ ሐምሌ በሮሜም ወሮች ወደ መስከረም ይሆናል ከአሥራሦስቱ ስድስት ከዕብራይስጥና ከሮማይስጥ ከመባቻ ስድስት ቀን ይቀርልሀል፡ በሰርቅ አንድ ናቸው የወሮቻቸው ስም ግን በየአጠራራቸው ነው፡፡ ስለዚህም ሁለቱ ወንጌላውያን ጌታ ወደ ታቦር ተራራ ከመውጣቱ አስቀድሞ እውነት እውነት እላችኋለሁ በዚህ ከቆሙት የእግዚአብሔርን መንግሥት እስኪያዩት

www.ethiopianorthodox.org

እብለክሙ ሀለዉ ዝየ እምእለ ይቀውሙ እለኢይ ጥዕምዎ ለሞት እስከ አመ ይሬእይዎ ለመንግሥተ እግዚአብሔር።

፳፫ ማቴዎስ ወማርቆስ ኖለቁ መዋዕለ እምሠርቀ ወርኀ ኀምሳይ ዘዕብራውያን እስመ ዕርገተ ደብረ ታቦር ወኮነ ሎሙ ሰዱሰ መዋዕለ።ወበእንተዝ ይቤሉ ወአመ ሰዱስ ነሥኦሙ። ወሉቃስኒ ኖለቈ መዋዕለ እምአመ ዘይቤ እግዚእ ኢየሱስ በደወለ ቂሳርያ ዘፊልጶስ አማን እብለክሙ ሀለዉ ዝየ እምእለ ይቀውሙ እለ ኢይጥዕምዎ ለሞት እስከ አመ ይሬእይዎ ለመንግሥተ እግዚአብሔር፡ እስከ አመ ተሰብሐ ኅብረ ገጹ በደብረ ታቦር በቅድመ ጴጥሮስ ወያዕቆብ ወዮሐንስ ወኮነ ሎቱ ሰሙነ መዋዕለ ። ወበእንተዝ ይቤ ወእም ድኅረ ዝንቱ ነገር በሳምንት ዕለት ነሥኦሙ ለጴጥሮስ ወለያዕቆብ ወለዮሐንስ ወዐርገ ደብረ ይጸሊ።ወእንዘ ይጼሊ ተወለጠ ርዕየተ ገጹ።

፳፬ ናሁኬ ዜና ሰላም በኀበ ወንጌላውያን ወአልቦ ስምዐ ሐሰት ውስተ ቃሎሙ ወባሕቱ አሌ ሎሙ ለእለ ይመይጥዎ ለቃለ መጻሕፍት ኀበ ግዕዞሙ ለኢሉብዎ።

፳፭ ወካዕበመ ለምንትኬ አስተጋብአ እግዚእነ ኀበ ደብረ ታቦር ፩ ድንግለ እምነቢያት ወ፪ ደናግለ እም ሐዋርያት ፩ መዓስበ እም ነቢያት ወ፩ እም ሐዋርያት ወከዊነ ርእሰ ቆመ ኀበ ውሉባን። ሙሴ ርእሶሙ ለነቢያት ወጴጥሮስ ርእሶሙ ለሐዋርያት። በእንተ ምንትኬ ኮነ ዝ እስመ ሥርዓተ ጥበቢሁ ለእግዚአብሔር ከመ ኢይትመከሑ ደናግል ላዕለ ውሉባን።ወመሀይምናንሂ ከመ ኢይበሉ ኢይክውኖ ለውሉብ ከዊነ ኤጲስቆጶስ። አኮ አስተሐቂሮ እግዚአብሔር ኃይለ ድንግልና ዘገብረ ዘንተ አላ ከመ ይግዝር ቊልፈተ ትምክሕት እምአልባበ ደናግል። እስመ ያፈቅሮ እግዚአብሔር ለዘማዊ ዘይላሑ በእንተ ኃጢአቱ እምድንግል ዘይትሜካሕ በድንግልናሁ።

፳፮ ምንተ ይበቊዕ ፈትለ ማኅቶት ዘእንበለ ቅብዕ :ወትጋህ ም ወጸሎት ዘእንበለ የውሃት፡ወዴግና ቤተክርስቲያን ዘእንበለ ምሕረተ ነዳያን ወድንግልና ዘእንበለ ትሕትና። አኮ ዘተረክበ ዓመፃ በኀበ ያዕቆብ ወዮሐንስ። እን በይነ ትምክሕት ዘያግሕሦሙ እምከዊነ ርዕስ። እመሰ ቦሙ ዐመፃ እምኢያርፈቆሙ ውስተ ሕፅኑ አላ ሠርዐ ላቲ ለቤተክርስቲያን ከመ ለዝሉፉ ዘእንበለ አዕብዮ ርእስ ተሀሉ። ዘሂ ተደንገለ ከመ ኢይትመካሕ ላዕለ ዘኢተደንገለ።

ድረስ ሞትን የማይቀምሱት አሉ ማለትን እንዳስቀደመ ተናገሩ።

፳፫ ማቴዎስና ማርቆስ ከዕብራውያን አምስተኛ ወር መባቻ ወደ ታቦር ተራራ እስከ ወጡበት ድረስ ያሉትን ቀኖች ቆጠሩ ስድስት ቀንም ሆነላቸው ስለዚህም በስድስተኛው ቀን ወሰዳቸው አሉ። ሉቃስም ጌታ ኢየሱስ በፊልጶስ ዘቂሳርያ አውራጃ እውነት እውነት እላችኋለው በዚህ ከቆሙት መካከል የእግዚአብሔርን መንግሥት ሳያዩ ሞትን የማይቀምሱ አሉ ካለበት ቀን ጀምሮ የፊቱ መልክ በታቦር ተራራ በጴጥሮስና በያዕቆብ በዮሐንስም ፊት ብርሃን እስከሆነበት ቀን ድረስ ያሉትን ቀኖች ቆጠረ፡ ስምንት ቀን ሆነለት፡ስለዚህም ከዚህም ነገር በኋላ በስምንተኛው ቀን ጴጥሮስንና ያዕቆብን ዮሐንስንም ይዟቸው ሊጸልይ ወደ ተራራ ወጣ ሲጸልይም መልኩ ተለወጠ አለ።

፳፬ እነሆ በወንጌላውያን ዘንድ የሰላም ዜና አለ በቃላቸውም የሐሰት ምስክርነት የለም ነገር ግን ባለማስተዋል የመጻሕፍትን ቃል እንደ አሳባቸው የሚተረጉሙት ወዮላቸው።

፳፭ ዳግመኛም ጌታችን በታቦር ተራራ ለምን ከነቢያት አንድ ድንግል ከሐዋርያት ም ሁለት ደናግልን ከነቢያት አንድ ያገባ ከሐዋርያትም አንድ ያገባ አመጣ አለቅነት ግን ባገቡት ዘንድ ጸና። ሙሴ የነቢያት አለቃ ጴጥሮስም የሐዋርያት አለቃ ነው ይህ ስለምን ሆነ ደናግል ባገቡት ላይ እንዳይመኩ እግዚአብሐር በጥበቡ ያደረገው ሥርዓት ነውና። ምእመናንም ያገባ ኤጲስቆጶስ መሆን አይቻለውም እንዳይሉ ነው። እግዚአብሔር ይህን ያደረገው የድንግልና ክብር አቃልሎ አይደለም የመመካትን ሽለፈት ከደናግል ልብ ያስወግድ ዘንድ ነው እንጂ እግዚአብሔር በድንግልናው ከሚመካ ድንግል ይልቅ ስለ ኃጢአቱ የሚያለቅሰውን አመንዝራ ይወዳልና።

፳፮ የመብራት ፈትል ያለ ዘይት በጾምና በጸሎት መትጋትስ ያለ የዋህነት ቤተክርስቲያንንም መከተል ለድሆች ያለመራራት ድንግልናም ያለ ትሕትና ምን ይጠቅማል። ስለ መመካትም ከአለቅነት ያራቃቸው በያዕቆብና በዮሐንስ ዓመፃ ተገኝቶ አይደለም። ዓማፃስ ቢኖርባቸው በእቅፍ ባላስቀመጣቸው ነበር ዘወትር ራስን ከፍ ያለማድረግ ትኖር ዘንድ ለቤተክርስቲያን ሥርዓት ሠራላት እንጂ ድንግል የሆነውም ድንግል ባልሆነው ላይ እንዳይመካ።

፳፯ ወዘሂ ኢተደንገለ ከመ ይነጽሮ በሥርዓተ መላዕክት ለዘተደንገለ በከመ አክበሮ ጴጥሮስ ለዮሐንስ በትእዛዘ ቀኖናሁ ወይቤሎ ለቀሌምንጦስ በዕለተ እሑድ ወበበ ዓላት ያንብቡ ውስተ ምሥዋዕ ወንጌለ ዮሐንስ እስመ ዘመለኮት ይትናገር ወጥንተ ሲኖዶስኒ ዘጉባኤ ሐዋርያት አመ ሠርዑ ትዕዛዘ ለመሀይ ምናን ለለ፩፩ በከመ ይደሉ ይቤሉ ኵሎሙ ሐዋርያ ከመ ዮሐንስ ይበል ይቅድም:: ዝ ውእ ቱ ዕሤተ ድንግልና ወንጽሕና ወረኪበ ሞገስ በቅድመ አኃው ወባቊዕ በኀበ እግዚአብሔር::

፳፰ ንግባእኬ ኀበ ጥንተ ዜና ዘይቤ እግዚእነ ሀለዉ ዝየ እለ ይቀውሙ እለ ኢይ ጥዕምዎ ለሞት እስከ አመ ይሬእይዎ ለመን ግሥተ እግዚአብሔር:: ዘንተ ይቤ በእንተ ጴጥሮስ ወያዕቆብ ወዮሐንስ እለ ርእዩ ስብ ሐቲሁ በደብረታቦር:: እመቦ ዘይቤ በእንተ ምጽአተ ክርስቶስ ተብህለ ዝ ጥዕሙኬ ሞተ ሐዋርያት እምቅድመ ምጽአተ ክርስቶስ:: ጴጥ ሮስኒ በዲበ መስቀል ወያዕቆብኒ ዘበሰይፍ ወኵሎሙ ሐዋርያት ለለ ፩ ፩ በከመ ከፈ ሎሙ ሥምረተ እግዚአብሔር ጥዕሙ ሞተ:: ዘይቤሰ እስከ አመ ይሬእይዎ ለመንግሥተ እግዚአብሔር ተፈጸመ ዘስብሐቲሁ ዘአስተርአየ በደብረ ታቦር::

፳፱ ምንትኬ ውእቱ ስብሐቲሁ ዘአስተርአየ በደብረ ታቦር ዘእንበለ ብርሃነ ስብሐቲሁ ዘለብሶ አዳም አመ ዕለተ ፍጥረቱ እስከ አመ ዕለተ ፀአቱ እምገነት:: ወይእዜኒ እለሰ አሥመርዎ ለእግዚአብሔር አመ ትንሣኤ ምዉታን ይእተ ሥነ መደንግፀ ይለብሱ ወይእ ተ ሞጣሕተ ዘመብረቀ ስብሐት ይተዓፀፉ:: በከመ ተርጐመ ቄርሎስ ልሳነ ሰይፍ ሊቀጳጳ ሳት ዘእለእስክንድርያ::

፴ ወካዕበመ ረከብኩ ዜና እንተ ትከውን ምክሐ ለገቢረ ዝንቱ በዓል ረከብክዎ ለ፩ ቀሲስ ዘአርማንያ ተሰአልክዎ ወእቤሎ መኑ ሐዋርያ ሰበከ ብሔረክሙ:ወአውሥእ ወይቤለኒ ሐውጾሰ ሐወጽዋ ጴጥሮስኒ ወጳው ሎስኒ ወፍጻሜ እምነታሰ ኮነ በስብከተ ሉቃስ ወንጌላዊ::

፴፩ ወካዕበ ተሰአልክዎ ወእቤሎ ትወድዩኑ ዔወ ወዘይተ ውስተ ቍርባንክሙ በከመ ሥርዓተ ቍርባን ዘሶርያ::አውሥአ ወይ ቤለኒ ንሕነሰ ኢናዐርግ ቁርባነ ዘእንበለ ኅብስተ ሥርናይ ንጹህ ወጽዋዓ ወይን ዘቱሱሕ ምስለ ማይ በከመ ቶስሐ እግዚእነ ወይነ ወማየ ወመ ጠዎሙ ለአርዳኢሁ::ወዓዲ ተሰአልክዎ ወእቤ ሎ ቦኑ ውስተ መጻሕፍቲክሙ ዘይነግር ከመ

፳፯ ድንግል ያልሆነውም ጴጥሮስ በቀኖናው ትእዛዝ ዮሐንስን እንዳከበረው ድንግ ሉን በመላእክት ሥርዓት እንዲያየው ሥር ዓት ሠራ ቀሌምንጦስንም በእሑድ ቀንና በበዓ ላት በመሠዊያው ላይ የመለኮትን ነገር ይናገ ራልና የዮሐንስን ወንጌል ያንብቡ አለው:: በሐ ዋርያት ጉባኤ በሲኖዶስም መጀመሪያ ለምእ መናን ለእያንዳንዱ እንደሚገባ ትእዛዝ በሠሩ ጊዜ ሐዋርያት ሁላቸው ዮሐንስ አስቀድሞ ይና ገር አሉ:: በወንድሞች ፊት ሞገስን በእግዚ አብሔርም ዘንድ ረብ ማግኘት የድንግልናና የንጽህና ዋጋ ይህ ነው::

፳፰ ጌታችን በዚህ ከቆሙት መካ ከል የእግዚአብሔርን መንግሥት እስኪያዩት ድረስ ሞትን የማይቀምሱት አሉ ስላለው የዜና ው መጀመሪያ እንመለስ::በታቦር ተራራ ክብ ሩን ስላዩ ለጴጥሮስ ስለ ያዕቆብ ስለ ዮሐንስም ይህን ተናገረ::ይህ የተነገረው ስለ ክርስቶስ መምጣት ነው የሚል ካለ ከክርስቶስ መምጣት በፊት እኮ ሐዋርያት ሞቱ ጴጥሮስም በመስ ቀል ላይ ተሰቅሎ ያዕቆብም በሰይፍ ተመትሮ ሐዋርያትም ሁላቸው እያንዳንዳቸው የእግዚአ ብሔር ፈቃድ እንዳደላቸው ሞትን ቀመሱ የእግዚአብሔርን መንግሥት እስኪያዩት ድረስ ያለው ግን በታቦር ተራራ ክብሩ በተገለጠ ጊዜ ተፈጽሟል::

፳፱ አዳም ከተፈጠረበት ቀን አንሥቶ ከገነት እስከወጣበት ቀን ድረስ ከለበሰው የክ ብሩ ብርሃን በቀር በታቦር ተራራ የተገለጠ ክብ ር ምንድር ነው::አሁንም እግዚአብሔርን ያገለ ገሉት በሙታን መነሣት ጊዜ ያን የሚያስደ ነግጥ መብረቅ ግምጃ ይጐናጸፉሉ:የሰይፍ ስለት የሆነ የእስክንድርያ ሊቀጳጳሳት ቄርሎስ እንደ ተረጐመው::

፴ ዳግመኛ ይህንን በዓል ለማድረግ መመኪያ የምትሆን ዜና አገኘሁ:: አንድ የአርማንያ ቄስ አገኘሁ በሀገራችሁ ያስተማረ ሐዋርያ ማን ነው ብዬ ጠየቅሁት እርሱም መልሶ መጐብኘትን ጴጥሮስም ጳውሎስም ጐብኝተዋታል የእምነቷ ፍጻሜ ግን በወንጌላዊ ሉቃስ ስብከት ነው አለኝ::

፴፩ ሁለተኛ እንደ ሶርያ የቁርባን ሥርዓት ቁርባናችሁ ውስጥ ጨውና ዘይት ትጨምራላችሁን ብዬ ጠየቅሁት እርሱም መልሶ እኛስ ከንጹህ የስንዴ ኅብስት ጌታችን ወይንና ውኃ ቀላቅሎ ለደቀመዛሙርቱ እንደሰ ጣቸው ውኃ ከተቀላቀለበት የወይን ጽዋ በቀር እናሳርግም አለኝ::ከእንደገናም በመጽሐፎቻችሁ

ሠደዩ ሐዋርያት ዜወ ወዘይተ ውስተ ቍርባኖሙ፡፡ ወእምዝ ተፈሥሐ ውእቱ ቀሲስ ዘአርማንያ በእንተ ዘአናኀኩ ማኅሠሠ ዘሥርዓተ ምሥጢር ወአውፅአ መጽሐፈ እም ውስ ተ ሕፅኑ እንተ ትነግር ዜና ሐዋርያት ንጹ ሐን፡ወቀልዓ ለይእቲ መጽሐፍ እንተ ትጽሕ ፈት በኖኅያተ አርማንያ፡፡ ወአኀዘ ያይድዓኒ እንዘ ያቀድም አንብቦቶ ወያተሉ ሊተ ተርጕ ሞቶ፡፡ ወይቤለኒ እም አመ መጠዎሙ እግዚእ ለአርዳኢሁ በሌሊት እንተ ባቲ ይእኀዝዎ ኅብስተ ወወይነ እንዘ ይብል ዝ ኅብስት ሥጋየ ወዝ ጽዋዕ ደምየ፡፡እምአሜሃ ኢነሥኡ ሐዋር ያት ቅድሳተ ምሥጢር እስከ በዓለ ደብረ ታቦር፡፡ ወበበዓለ ደብረታቦር ሜምዎ ለያዕቆብ እኁሁ ለእግዚእነ ኤጲስቆጶስ ዘኢየሩሳሌም ወአዘዝዎ ከመ ያዕርግ ቍርባነ ወአዕረገ ውእ ቱኒ ውስተ ምሥዋዕ ኅብስተ ንጹሐ ዘእንበለ ዜው ወዘይት ወቶስሐ ማየ ወወይነ ወሦጠ ውስጠ ጽዋዕ ወአቍረቦሙ ለሐዋርያት በከመ ገብረ እግዚእነ፡፡

፴፪ ወዓዲ ነገረኒ እንዘ ይብል ማቴዎስ ወንጌላዊ ጸሐፈ ወንጌለ በ፰ ዓመት እምዕርገተ እግዚእነ፡፡ ማርቆስ ወንጌላዊ ጸሐፈ ወንጌለ በ፲ወ፪ ዓመት እምዕርገተ እግዚእነ፡፡ ሉቃስ ወንጌላዊ ጸሐፈ ወንጌለ በ፳ወ፪ ዓመት እምዕ ርገተ እግዚእነ፡፡ዮሐንስ ወንጌላዊ ጸሐፈ ወንጌለ በ፴ ዓመት እምዕርገተ እግዚእነ፡፡

፴፫ ወአነሂ በምክንያተ ዝንቱ ነገር ረከብኩ ውስተ መጻሕፍቲነ ዘይብል ከመዝ ቀሌምንጦስ ጸሐፈ ሥርዐተ ቤተ ክርስቲን ዘው እቱ ትምህርተ ዲድስቅልያ ፩ እስመ ይቤሉ ሐዋርያት ጸሐፍነ ዘንተ መጽሐፈ ትግሣጽ ወፈኖነ ምስለ ቀሌምንጦስ እኁነ ላእክ ለዝንቱ ዓለም፡፡ወሲኖዶስ እንተ ሐዋርያት ፯ ተፈሥሑ ኦ ውሉድነ፡ ስምዖን ቀነናዊ ፪ አብጥሊስ ፫ እምድኅረ ዐርገ ፬ ፡ሥርዓተ ሀብት በእተ እለ ይጠመቁ ፭፡ በእንተ ከመ ፩ ኮናኒ ፮ ፡ትእዛዝ ዘአዘዞ ጴጥሮስ ለቀሌምንጦስ ፯፡፡ ወበእንተዝ ይቤሉ መጽሐፈ ቀሌምንጦስ ምስለ ሲኖዶስ ፰፡፡ ለእመሰ ይብልዎ መጽሐፈ ቀሌምንጦስ እንተ ባሕቲቱ ፰ ክፍል ለእመ ተደመረ መጽ ሐፈ ሲኖዶስ ፯ ይከውን ፲ወ፭ ክፍለ ወበዝ ይት ዐወቅ ሐሰቶሙ ለእመ በዝን እምዝ ፰ ክፍል ዘአወፈዩነ በትላቄ፡፡ወለይእቲሰ መጽሐፈ ሐሰ ቶሙ ጴጥሮስኒ ኢነበባ ወቀሌምንጦስኒ ኢጸ ሐፉ አላ ይስሐቅ ትግራይ መሣጤ ጽጽስና ከመ ሚሊጢስ ወሚመተ ጽጽስናሁኒ እምኅበ መለካ ውያን ውእቱ፡፡ወበእንተዝ ነኪር ትምህርቱ እም ት ምህርትነ ወመጻፍቲሁ እመጻሕፍቲነ፡እስመ እመዝገበ ሐሰትረከቦ ወበቃለ ሐሰት አፅለም፡፡

ሐዋርያት በቁርባናቸው ውስጥ ጨውና ዘይት እንደጨመሩ የሚናገር አለን ብዬ ጠየቅሁት፡፡ ከዚህ በኋላ የአርማንያው ቄስ ስለምሥጢር ሥርዓት መጠየቅን ስላበዛሁ ደስ አለው ከእቅ ፉም ንጽህን የሆኑ የሐዋርያትን ዜና የምት ናገር መጽሐፍ አወጣ በአርማንያ ፊደሎች የተጻፈችይቱንም መጽሐፍ ገለጣት ማንበብን እያስቀደመ መተርጐሙን እያስከተለ ሊነግረኝ ጀመረ እንዲህም አለኝ በተያዘባት ሌሊት ይህ ኅብስት ሥጋዬ ነው ይህም ጽዋ ደሜ ነው ብሎ ኅብስትና ወይን ከሰጣቸው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሐዋርያት እስከ ደብረታቦር በዓል ድረስ የተቀደሰውን ምሥጢር አልተቀበሉም፡፡ በደብረታቦር በዓል የጌታችን ወንድም ያዕቆብን ቁርባን ያሳርግ ዘንድ የኢየሩሳሌም ኤጲስቆጶስ አድርገው ሾሙት፡፡ እርሱም ጨውና ዘይት የሌለው ንጹህ ኅብስትን በመሠዊያ ላይ አሳረገ ውኃና ወይንም ቀላቅሎ በጽዋው ጨመረ ጌታችንም እንዳደረገ ሐዋርያትን አቆረባቸው፡፡

፴፪ ዳግመኛም ወንገላዊ ማቴዎስ ጌታችን ባረገ በዘጠነኛ ዓመቱ ወንጌልን ጻፈ፡ ወንጌላዊ ማርቆስ ጌታችን ባረገ በአሥራ ሁለተኛ ዓመት ወንጌልን ጻፈ፡፡ ወንጌላዊ ሉቃስ ጌታችን ካረገ በሃያሁለተኛ ዓመት ወንጌላዊ ዮሐንስም ጌታችን ባረገ በሠላሳ ዘመን ወንጌልን ጻፈ አለኝ፡፡

፴፫ እኔም በዚህ ነገር ምክንያት በመጽሐፎቻችን ውስጥ እንዲህ የሚል አገኘሁ ቀሌምንጦስ የቤተክርስቲያንን ሥርዓት ጻፈ ይኸውም አንዱ የዲድስቅልያ ትምህርት ነው፡፡ ሐዋርያት ይህንን የተግሣጽ መጽሐፍ ጽፈን ለዚህ ዓለም መልእክተኛ ቢሆን በወንድማችን በቀሌምንጦስ እጅ ላክን ብለዋልና፡፡ የሐዋርያት ሲኖደስም ሰባቱ ናቸው ልጆቻችን ሆይ ደስ ይበላችሁ አንድ፡ ቀነናዊው ስምዖን ሁለት፡ አብ ጥሊስ ሦስት፡ ካረገ በኋላ አራት፡ ስለሚጠመቁ ሰዎች የጸጋ ሥርዓት አምስት፡አንድ ገዥ እንዳ ለ ስለሚናገር ስድስት፡ ጴጥሮስ ቀሌምንጦስን ያዘዘው ሰባት፡፡ስለዚህም የቀሌምንጦስን መጽሐ ፍ ከሲኖዶስ ጋር ስምንት አሉ፡፡ የቀሌምንጦ ስን መጽሐፍ ብቻውን ስምንት ክፍል ነው ቢሉ ሰባት መጻሕፍተ ሲኖዶስ ሲጨመሩ አሥ ራ አምስት ክፍል ይሆናል፡፡ይኸችን የሐሰ ታቸው መጽሐፍ ግን ጴጥሮስ አልተናገራትም ቀሌምንጦስም አልጻፋትም እንደሚሊጢስ ጵጵ ስናን የነጠቀ ይስሐቅ ጨመራት እንጂ ፡ የጵጵስናውም ሹመት ከመለከውያን ዘንድ ነው ፡፡ ስለዚህም ትምህርቱ ከትምህርታችን መጽሐፎቻቸውም ከመጽሐፎቻችን የተለዩ ናቸው ከሐሰት መዝገብ አግኝቶታል በሐሰትም ቃል ቀድቷታልና ፡፡

፴፬ ወይእዜኒ ንግባእ ኀበ ዜና ወንጌላውያን ታዴዎስ ወቀለዮጺ።ወንጌለ ዘሰበከ ማቴምስ በልሳነ ዕብራውን በኢየሩሳሌም ተርጐሙ በነገረ ጽርእ ምስለ ዮሐንስ።ወንጌለ ዘማርቆስ ጴጥሮስ ተርጐመ በነገረ ጽርእ በሀገረ ሮሜ። ወንጌለ ዘሉቃስ ተርጐመ ካልኡ ሉቃስ በነገረ ጽርእ እስመ ረድኡ ውእቱ ለጳውሎስ ወከመዝ ጸሐፈ እንዘ ይብል አምኃክሙ ሉቃስ ዐቃቤ ሥራይ ፍቁርየ። ወግብረ ሐዋርያት ሉቃስ ወንጌላዊ ተርጐመ በነገረ ጽርእ እንዘ በዕብራይስጢ ሀለወ።ወንጌለ ዮሐንስ ተርጐመ ዮሐንስ ጳጳስ በነገረ ጽርእ።

፴፭ ወይእዜኒ ንጸውዖሙ ለነቢያት ወለሐዋርያት ለገቢረ ዝንቱ በዓል። ንበሎሙ ለነቢያት ንዑኬ ኦ ነቢያተ እግዚአብሔር ምስለ ሙሴ ወኤልያስ ለገቢረ ዝንቱ በዓል። ንዑ ሐዋርያተ ኢየሱስ ክርስቶስ ምስለ ጴጥሮስ ወያዕቆብ ወዮሐንስ ገቢረ ዝንቱ በዓል። ነዓ ኦ ዳዊት ነቢይ ከመ ትበል ደብረ እግዚአብሔር ደብር ጥሉል። ደብር ርጉዕ ወደብር ጥሉል። ነዓ ኢሳይያስ ነቢይ ከመ ትበል መኑ የዐርግ ውስተ ደብረ እግዚአብሔር ይንግሩነ ፍኖቶ ወንሑርቤቶ።

፴፮ ወአንተኒ ጴጥሮስ እፎኬ ለሙሴ ወ፩ ለኤልያስ። ወለከሰ እምኔሰከ ከመ ትንበር ህየ እንዘ ትሬኢ ስነ ወትብሉ ለወልደ እግዚአብሔር ሊቅ ይኄይሰኒ ንንበር ዝየ ወንግበር ፫ ሰቃልወ ፩ ለከ ወ፩ አዳም ዘቀዲሙ እንዘ ትትፌሣሕ በብርሃነ ገጹ ለዘተሠገወ እምወለተ አዳም።ለእመ ነበርከሙ ህየ በገጸ መኑ ትድኅን ቤተ ክርስቲያን ዘእንበለ በጽፍዓተ መላትሒሁ ለዘተሰብሐ ኀብረ ገጹ በደብረ ታቦር። ለእመ ነበርከሙ ህየ እደ መኑ ይትቀነው በዲበ መስቀል በቀራንዮ ለመድኃኒተ ዓለም።እምገቦ መኑ ይውኅዝ ማየ ሕይወት ኀበ መቃብሪሁ ለአዳም።

፴፯ ለእመ ነበርከሙ ህየ መኑ ይጥዕም ሞተ በሥጋ ከመ ይኩን ሕይወተ ምውታን ወመኑ ይክል አውፅኦቶሙ ለፍሳተ ጻድቃን እምቀላየ ደይን። ለእመ ነበርከሙ ህየ መኑ ይትረሰይ ለቀትል ምስለ ሠራዊተ ጽልመት ከመ ይግበር ባእሰ ወመኑ ያነሥእ መራደ ዲበ ሠራዊተ ቤልሖር ከመ ያንግፎሙ ለአሕዛብ እምአምልኮ ጣዖት። ለእመ ነበርከሙ ህየ መኑ የሐንጻ ለቤተክርስቲያኑ ዲቤከ ወያቀውም አዕማዲሃ ሐዋርያተ ወአናቅጺሃ ነቢያተ ወአረፋቲሃ ሰማዕታተ። ለእመ ነበርከሙ ህየ መኑ ይፌንወከሙ ውስተ ኵሉ አጽናፈ ዓለም ወይብለከሙ ሑሩ ወስብኩ ወንጌለ መንግሥት ውስተ አጽናፈ ዓለም። ወእንዘ ታጠምቅዎሙ

፴፬ አሁንም ወደወንጌላውያን ታዴምስና ቀለዮጳ ዜና እንመለስ።ማቴምስ በዕብራውያን ቋንቋ የሰበከውን ወንጌል በኢየሩሳሌም ከዮሐንስ ጋር በጽርዕ ቋንቋ ተረጐሙ፡ የማርቆስን ወንጌል ጴጥሮስ በሮም ሀገር በጽርዕ ቋንቋ ተረጐመው እርሱም የጳውሎስ ደቀመዝሙር ነው ባለመድኀኒት ወዳጄ ሉቃስ ሰላም ይላችኋል ብሎ ጻፈ።የሐዋርያት ሥራንም ወንጌላዊ ሉቃስ በዕብራይስጥ ተጽፎ ሳለ በጽርዕ ቋንቋ ተረጐመው የዮሐንስ ወንጌልንም ጳጳስ ዮሐንፋ በጽርዕ ቋንቋ ተረጐመው።

፴፭ አሁንም ይህን በዓል ለማድረግ ነቢያትና ሐዋርያትን እንጥራቸው፡ነቢያትን የእግዚአብሔር ነቢያት ሆይ ይህን በዓል ለማድረግ ከሙሴና ከኤልያስ ጋር ኑ እንበላቸው፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት ሆይ ከጴጥሮስና ከያዕቆብ ከዮሐንስም ጋር ይህን በዓል ለማድረግ ኑ እንበላቸው።ነቢዩ ዳዊት ሆይ የእግዚአብሔር የለመለመ ተራራ ነው የረጋ የለመለ ተራራ ትል ዘንድና።ነቢዩ ኢሳይያስ ሆይ ወደ እግዚአብሔር ተራራ ማን ይወጣል መንገዱን ይነግሩን ዘንድ ወደ ቤቱም እንሄድ ዘንድ እንድትልና።

፴፮ አንተም ጴጥሮስ ሆይ የእግዚአብሔርን ልጅ እንደምን መምህር ሆይ በዚህ እንኖር ዘንድ ይሻላልና ሦስት ሰቀላዎችን እንሥራ አንዱን ለአንተ አንዱን ለሙሴ አንዱን ለኤልያስ አልኸው፡ ለአንተስ የቀደመውን የአዳምን ደምግባት አይተህ ከአዳም ሴት ልጅ በሥጋ በተወለደው በፊቱ ብርሃን እየተደሰትህ በዚያ ትኖር ዘንድ በተሻለህ ነበር እናንተ በዚያ ኖራችሁ ቢሆን የፊቱ መልክ በታቦር ተራራ ብርሃን በሆነው በእርሱ በጉንጮቹ በጥፊ መመታት ካልሆነ በቀር ቤተክርስቲያን በማን ፊት ትድን ነበር።

፴፯ እናንተ በዚያ ከኖራችሁ በቀራንዮ ተራራ በመስቀል ላይ ለዓለም መዳን ማን እጁን ይቸነከር ነበር ከማን ጐን የሕይወት ውኃ ወደአዳም መቃብር ይፈስስ ነበር እናንተ በዚያ ከኖራችሁ ለሙታን ሕይወት ይሆን ዘንድ ማን በሥጋ ሞትን ይቀምስ ነበር ማንስ የጻድቃንን ነፍሶች ከአንጦርጦስ ሊያወጣቸው ይችል ነበር።እናንተ በዚያ ኖራችሁ ቢሆን ጦርነትን ያደርግ ዘንድ ማን ከጨለማ ሠራዊት ጋር ለመዋጋት ይዘጋጅ ነበር አሕዛብን ከጣዖት አምልኮ ይታደጋቸው ዘንድ በቤልሆር ሠራዊት ላይ ማን ጦረኛ ያስነሳ ነበር።እናንተ በዚያ ኖራችሁ ቢሆን ማን ቤተክርስቲያኑን በአንተ ላይ ይሠራት ምሰሶዎቿ ሐዋርያትን በሮቿ ነቢያትን ግድግዳዎቿ ሰማዕታትንስ ማን ያቆም ነበር።እናንተ በዚያ ኖራችሁ ቢሆን ማን ሂዱና በዓለም ዳርቻዎች

ባሉ ብስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ::

ሁሉ የመንግሥትን ወንጌል አስተምሩ ስታጠምቁአቸውም በአብና በወልድ በመንፈስቅዱስም ስም በሉ ብሎ ይልካችሁ ነበር::

፴፰ ወለከሰ ይደልወከ ኦ አቡነ ጴጥሮስ ከመ ተሀሉ ምስሌነ ለገቢረ በዓል ወተጠይቀነ ስምዐ ጽድቅ ዘሰማዕከ እምኀበ አብ ዘከመ ስምዐ ኮነ ላዕለ ወልዱ::ወበል ይእዜኒ በከመ ትቤ በመልእክትከ ዳግሚት ቃል ወረደ ላዕሌሁ እምውስተ ዕበየ ክብረ ስብሐቲሁ ይቤ ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ዘአነ ኀረይኩ:: ዘንተ ቃለ ንሕነ ሰማዕናሁ ከመ እምሰማይ ወረደ ሎቱ እንዘ ሀሎነ ምስሌሁ በደብረ መቅደሱ::

፴፰ አባታችን ጴጥሮስ ሆይ አንተስ በዓል ለማድረግ ከእኛ ጋር ልትሆን ስለልጁ እንደመሰከረ ከአብ ዘንድ የሰማኸውን ታስረዳን ዘንድ ይገባሀል በሁለተኛይቱ ከፍጹም የክብሩ ጌትነት ቃል ወደ እርሱ መጣ ይህ የምወደው እኔም የመረጥሁት ልጀ ነው አለ ይህንን ቃል ከእርሱ ጋር በመቅደሱ ተራራ ሳለን ከሰማይ እንደወረደለት እኛ ሰማነው እንዳልህ ዛሬም በል::

፴፱ ወስነሰ ዘለብሰ እግዚእነ በመል ዕልተ ደብረታቦር አኮ ስነ መለኮት ዘአስተርአየ እምአድለቅለቃ ለምድር ወእምሆካ ለቀላይ ወእመኢክህለ ዓለም አግምሮቶ:: ወይእቲሰ ሱራኄ ብርሃን::ብርሃነ ገጹ ይእቲ ለአዳም አመነበረ ውስተ ገነተ ኤዶም:: ወዓጽፈ መብረቅኒ ዘአደንገጾሙ ለአርድእት አራዘ መንግሥቱ ውእቱ ለአበ ኵልነ ዘአልበሶ እግዚአብሔር አመ አኰነኖ ላዕለ ኵሉ ፍጡራን እለ ውስተ ምድር:: ወአመ ዐለወ ትእዛዞ ለእግዚአብሔር ተግኅሠ ዓጽፈ ብርሃን እምኔሁ ወአስተርአየ ዕርቃኑ ወሰሰለ ማዕዝረ ስብሓት እምገጹ::

፴፱ ጌታችን በታቦር ተራራ ራስ ላይ የለበሰውም ብርሃን የመለኮት ብርሃን አልታየም የመለኮት ብርሃን የታየስ ቢሆን ምድርን ባነዋወጣት ባሕርንም ባናወጼት ዓለምም እርሱን መቻል በተሳነው ነበር እርሷ ግን የብርሃን ጸዳል አዳም ከኤዶም ገነት ውስጥ በነበረ ጊዜ የነበረችይቱ ብርሃን ናት:: ደቀመዛሙርትን ያስደነገጣቸው የመብረቅ ግምጃም እግዚአብሔር በምድር ላይ ባሉ ፍጥረታት ሁሉ ላይ ገዥ አለቃ ባደረገው ጊዜ ያለበሰው የሁላችን አባት (የአዳም)ልብሰ መንግሥት ነው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ባፈረሰ ጊዜ ግን የብርሃን ግምጃ ከእርሱ ተወሰደ ዕርቃኑ ተገለጠ የክብር ጮራም ከፊቱ ሸሸ::

፵ ሶበሰ ንገብር ፈቃዶ ለእግዚአብሔር ይእተ ስነ እምለበስነ እንተ ለብሰ መድኅን በመልዕልተ ደብረታቦር:: በከመ ይቤ እግዚእነ በወንጌል አሜሃ ይእተ አሚረ ይበርሁ ጻድቃን ከመ ፀሐይ በመንግሥተ አቡሆሙ ዘበሰማያት:: በእንተምንትኬ ለብሳ መድኅን ለብርሃነ አዳም በመልዕልተ ደብረታቦር:: ከመ ያርኢኑ ዕበየ ግርማሁ ለአርዳኢሁ:: ሐሰ ሎቱ:: እመሰ ፈቀደ ያርኢ ዕበየ ግርማሁ እምአርአየ ስነ መለኮቱ እስመ ብርሃነ ፀሐይ ወወርኅ ወንጥረ መባርቅት ኢኮነ መጠነ ቀለምጺጽ በኀበ ብርሃኑ ለመለኮተ አምላክነ:: ዘለብሰሰ ስኖ ለአዳም ከመ ይፈጽም ሥጋዌ እንተ አቡነ አዳም:: አመ ሕፃን ውእቱ ፈጸመ ሥርዓተ ሕፃናት በጠቢወ ጥብ ወሐቍቃፌ በአብራከ እም ወበድሒክ ውስተ መርኅብ ወበልሂቅ በበህቅ:: ወአመ ወርዘወሂ ፈጸመ ሕገ ወራዙት በርሂብ ወበጸሚእ በደኪም ወበሐፊው:: ወባሕቱ ተርፈቶ ትርሲተ አዳም ዘውስተ ገነት ወለይእቲኒ ፈጸማ በመልዕልተ ደብረ ታቦር ከመ ይኩን ፈጹመ ሥጋዌ ሁ በከመ ሥጋዌ አዳም::

፵ እኛም የእግዚአብሔርን ፈቃዱን ብናደርግስ መድኅን በታቦር ተራራ ራስ የለበሳትን ያችን ጸዳል እኛም በለበስናት ነበር ጌታችን በወንጌል ያን ጊዜ ጻድቃን በሰማያት ባለ በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ይበራሉ እንዳለ መድኅን የአዳምን ብርሃን ለምን በታቦር ተራራ ራስ ላይ ለበሳት የግርማውን ታላቅነት ለደቀ መዛሙርቱ ሊያሳይ ነውን አይደለም የግርማውን ታላቅነት ሊያሳይ ቢወድስ የመለኮቱን ብርሃን በገለጠ ነበር የፀሐይና የጨረቃን ብርሃን የመብረቆችም ብልጭታ በአምላካችን በመለኮት ብርሃን ዘንድ እንደእሳት ውልብልቢት ያህል አይደለምን::የአዳምን ጸዳል የለበሰው ግን የአባታችን የአዳምን ሥጋ ፍጹም ያደርግ ዘንድ ነው ::ሕፃን ሳለ ጡት በመጥባት በእናት ጭኖች ላይ በመታቀፍ በሜዳም ላይ በመዳህ በየጥ ቂቱም በማደግ የሕፃናትን ሥርዓት ፈጸመ ::ጐልማሳም በሆነ ጊዜ በመራብና በመጠ ማት በመድከምና በመውዛት የጐልማሶችን ልማድ (ሕግ)ፈጸመ:: ዳሩ ግን በገነት ውስጥ የነበረችው የአዳም ጌጥ ሽልማት ቀረችው እርሷንም ሰው መሆኑ እንደ አዳም ሰው መሆን ፍጹም ይሆን ዘንድ በታቦር ተራራ ራስ ላይ ፈጸማት::

፵፩ ለምንትኬ ዘኢያርአየ ስብሐቲሁ በቅድመ ጉባኤ አይሁድ እንዘ ይበርህ ገጹ ከመ

፵፩ ስለምን በአይሁድ ጉባኤ ፊት ፊቱ እንደ ፀሐይ አብርቶ ልብሱም በሰማይ

ፀሐይ ወእንዘ ይበርቅ አልባሲሁ ከመ ብርሃን ዘለንጳስ ዘያንበለብል በገጸ ሰማይ። ዘንተሰ ከበተ እምሕዝበ እስራኤል ከመ ኢያእምርዎ ወከመ ኢያጽሪው ቀቲሎቶ በፍርሀተ ግርማሁ። ወእምአ ርዳኢሁኒ አኮ ለኵሎሙ ዘአዕረጎሙ ዘእንበለ ፫ እለ ኅረዮሙ።ወሎሙኒ አማኅፀና ሙ ከመ ኢይንግሩ ምሥጢረ ዘርእዩ፡ በከመ ይቤ ወንጌላዊ ወእንዘ ይወርዱ እምደብር አዘዞሙ ኢይንግሩ ወኢለመኑሂ ዘእንበለ አመ ትንሥአ ወልደ እጓለ እመሕያው። ርኢኬ ዘከመ ከበተ ስብሐቲሁ እምነገደ ሕዝባ ለእሙ እንዘ ይጽሕቅ ለሕማማተ መስቀል። ወአዘዞሙ ለአርዳኢሁ ኢይንግሩ እስከ አመ ትንሣኤ ምሥጢረ ስብሐቲሁ ዘርእዩ በደብረታቦር።

፵፪ ሎቱ ስብሐት ለዘበስብሐተ አቡሁ ይሴባሕ፡ ወሎቱ ቅድሳት ለዘበቅድሳተ መንፈሱ ይትቄደስ ለዓለመ ዓለም አሜን፤ ወአሜን።

፵፫ ተፈጸመ ዘለፋሆሙ ለረሲዓን፡ እለ ይትከሐዱ ትንሣኤ ምውታን በመትልወ ትም ህርቶሙ ለሰዱቃውያን፡ ጽኑዓነ ልብ ከመ አእባን።ሱቱፋነ ትምህርት ምስለ ረሲዓን፡ እንዘ ቦሙ ዐይነ እለ ኢየሬእዩ ከመ ዳጎን፡ ወእንዘ ቦሙ እዝን እለ ኢይሰምዑ ከመ አጵሎን፡ ይቤ ጊዮርጊስ ጽቡሰ ኀሊና ወድኩመ ልሳን፡ ዘበሃይማኖቱ እም ሕዝበ ናዝራውያን፡ ወበጥም ቀቱ ዐቢየ ክርስቲያን፡ስአሉ ሎቱ ሥርየተ ኃጣ ውኢሁ ሕዝብ መሲሐውያን፡ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፵፬ በስመ እግዚአብሔር ዘይሴብዖን ለምዕዋደ ሰንበታት፡ከመ ይኩና ለኵፋሌ መዋ ዕል ወለፍጻሜ ኢዮቤልዎሳት፡ ዘይሬብዖን ለከን ትሮሳተ ዓመታት፡ከመ ይኩና ለሐጋይ ወለክ ረምት፡ ለመጺው ወለተወን በዘይትወሀብ ዝናመ በረከት፡ ዘይኄምሶን ለኬክሮሳተ ሰዓታት፡ ከመ ይኩና መዐርገ ጸሎታት፡ ተፈጸመት ዛቲ መጽሐፍ እንተ አስተጋብእነ እምቃለ ኦሪት ወነቢያት፡ ወእምቃለ ወንጌል ወሐዋርያት። ወፍካሬ ነገራሰ በእንተ ሃይማ ኖት ርትዕት። ከመ ትኩን መርሐ ለዐዋው ርት፡በዘይትፈለጡ አግባዕ ወአግ ባዕት፡ እማበረ ቈናጽል ወተኳሉት፡ እምጉባኤ አሕርው ወአዝብእት፡ ዘውእቶሙ መምህራነ ሐሰት፡ እለ ሰጠጥዋ ለልብሰ ጥምቀት ወሰጸ ርዋ ለበትረ ክህነት፡ ዘውእቶሙ አንቀጸ ሲኦል እለ ያበውኡ ውስተ ገሃነመ እሳት፡ ኅበ ይልህብ ተይ ወዝፍት፡ ወማኅደርሙሂ ውስተ ጸናፌ ጽልመት፡ ወመከፈልቶሙኒ ምስለ ተንበላት፡ ወሱታፌሆሙኒ ምስለ ማኅበረ አጋንንት።

ጠፈር እንደ ሚንቦገቦግ የነበልባል ብርሃን እያብ ለጨለጨ ክብሩን አልገለጠም፡ ይህንንስ እንዳ ያውቁት ግርማውንም በመፍራት እርሱን መግ ደልን እንዳይተዉ ከእስራኤል ሰዎች ሸሸገ ከደ ቀመዛመርቱም ከመረጣቸው ከሦስቱ በቀር ሁላ ቸውን ወደተራራ ያወጣቸው አይደለም እነር ሱንም ወንጌላዊው ከተራራውም ሲወርድ የሰ ው ልጅ ከሙታን ሳይነሣ ለማንም ለማን እን ዳይነግሩ አደራ ሰጥቶአቸዋል የመስቀል መከ ራዎችን ለመቀበል ተግቶ ክብሩን ከእናቱ ወገኖች ነገድ እንደሸሸገ ተመልከት ደቀመዛሙ ርቱን እስከ ትንሣኤው ድረስ በታቦር ተራራ ያዩትን የክብሩን ምሥጢር እንዳይናገሩ አዘዛ ቸው።

፵፪ በአባቱ ምስጋና ለሚመሰገን ለእርሱ ምስጋና ይገባል በመንፈስ ቅድስና ለሚቀደስ ለእርሱ ምስጋና ይገባል ለዘላለሙ አሜን ይሁን።

፵፫ የሰዱቃውያንን ትምህርት በመከ ተል የሙታንን መነሳት የሚክዱ እንደ ደንጊ ያዎች ልባቸው የደነደነ ከመናፍቃን ጋር በት ምህርት የሚተባበሩ እንደ ዳጎን ዓይን ሳላቸው የሚያዩ ጆሮም እያላቸው እንደ አጵሎን የማይ ሰሙ የዝንጉዎች ተግሣጽ ተፈጸመ። ኅሊናው የተሰበረ አንደበቱ የደከመ በሃይማኖቱ ከናዝራ ውያን ወገን በጥምቀቱም ከዐቢየ ክርስቲያን ወገን የሆነ ጊዮርጊስ ተናገረው፡ መሲሐውያን የሆናችሁ ወገኖች ሆይ ስለ ኃጢአቱ ሥርየትን ለምኑለት ለዘላለሙ አሜን።

፵፬ ቀናትን ለመክፈል ኢዮቤልዩዎችንም ለመፈጸም ይረዳ ዘንድ የሰንበታትን መመላለሻ ሰባት ባደረገ ለበጋና ለክረምት ለበልግና ለጸደይ የበረከት ዝናምን በሚሰጥበት ገንዘብ የዓመ ታትን ከንትሮስ አራት ባደረጋቸው የጸሎቶ ችም ማስረጊያ ሊሆኑ የሰዓቶችን ኬክሮሳት አምስት ባደረጋቸው በእግዚአብሔር ስም በኦሪ ትና በነቢያት ቃል ከወንጌልና ከሐዋርያትም ቃል የሰበሰብናት ይህች መጽሐፍ ተፈጸመች፡ የነሯም ፍቺ ስለ ቀናች ሃይማኖት ነው ወንድ በጎችና ሴት በጎች ከቀበሮዎችና ከተኩላዎች አንድነት ከአሪያዎችና ከጅቦችም ጉባኤ ይለዩ ዘንድ ለዕውሮች መሪ ትሆን ዘንድ፡ እነዚሁም የጥምቀትን ልብስ የቀደዱአት የክህነትንም በትር የሰነጠቋት የሐሰት መምህራን ናቸው። እነርሱም ተይና ዝፍት ወደሚያ ቃጥልበት ወደ ገሃነም እሳት የሚያስገቡ የሲኦል በሮች ናቸው ማደሪያቸውም በጥልቅ ጨለማ ውስጥ ነው።እድል ፈንታቸውም ከእስላሞች ጋር ኅብረታቸው ከአጋንንት አንድነት ጋር ነው።

፵፭ ወፍጻሜሃሰ ለዛቲ መጽሐፈ ዘለፋሆሙ ኮነ በ፷፻ወ፱፻፴ወ፪ ዓመተ ምሕረት በሐሳበ ሮማውያን። በ፷፻ወ፱፻፳ ወ፬ በሐሳበ አፍራቅያ እንተ ይእቲ ቀዳሚተ ሮሜ ዘስብከተ ጴጥሮስ ወጳውሎስ። በ፷፻ ወ፱፻፲ወ፯ በሐሳበ ግብጻውያን ዘውእቶሙ እምስብከተ ማርቆስ ወንጌላዊ ዘሰበከ ሎሙ አመ ሳብዕ ዓመተ መንግሥቱ ለኔሮን ወሜመ ሎሙ አንያኖስሃ ኤጲስቆጶሰ። በ፷፻ወ፱፻፺ወ፪ በሐሳበ ኢትዮጵያ እንተ ይእቲ ቤተመቅደሱ ለእግዚአብሔር እንተ አምነቶ ዘእንበለ ሐዋርያ።

፵፮ ተፈጸመት ዛቲ መጽሐፍ በሣልስ ወርኅ ሐሳበ ዕብራውያን።ወበሐሳበ ግብጻውያን በዐሥር ወርኅ።አመ ፲ ዓመተ መንግሥቱ ለይስሐቅ አመ ፳ወ፯ ለወርኃ ጽዮን ዘውእቱ ሰኔ ወአመ፳ በሌሊት ወአመ ፳ወ፩ ለወርኃ ኃዚራን እምቅድመ ተሱዕ መዋዕል ለበአተ ተሙዝ ወስመ ወርኁሰ ዮልዮን በአውርኃ ሮሜ ኅቡረ ሠርቀ ምስለ ዘዕብራውያን። በ፲ወ፰ አበቅቴ በ፯ ጥንትዮን በ፫ እንድክትዮን በ፮ ጳጉሜት በ፪ ዕለት ዕለተ ዐውድ በመዋዕለ ዮሐንስ ወንጌላዊ እንዘ ሀሎነ በሀገረ ሰግላ በዕለተ ረቡዕ ጊዜ ፱ ሳዕ ዘመዐልት።

መልአ መጽሐፈ ምሥጢር ዘይነግር ሃይማኖተ በእንተ ሥላሴ፡ ወካዕበመ በእንተ ወልደ እግዚአብሔር ዘከመ ኮነ ብእሴ። ሎቱ ይደሉ ስብሐት ዘምስለ ውዳሴ፡ ለዓለመ ዓለም አሜን፡ ወአሜን።

.......... /// ..............

፵፭ የዚህች የተግሣጻቸውም መጽሐፍ የተፈጸመችው በሮማውያን ቁጥር በስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሠላሳ ሁለት ዓመተ ምሕረት፡ የሮሜ ፊተኛ ጴጥሮስና ጳውሎስ ያስተማሩባት በሆነች በአፍራቅያ አቆጣጠር በስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃያ አራት፡በኔሮን መንግሥት ሰባተኛ ዓመት ካስተማራቸው አንያኖስንም ኤጲስቆጶስ አድርጎ ከሾመላቸው ከወንጌላዊው ከማርቆስ ስብከት የተነሣ ባመኑ በግብጻ ውያን አቆጣጠር በስድስት ሺህ ዘጠኝመቶ አሥራ ሰባት ያለ ለሐዋርያ ባመነችው የእግዚአብሔር ቤተመቅደሱ በሆነች በኢትዮጵያ አቆጣጠር በስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ሁለት ነው።

፵፮ ይህች መጽሐፍ በዕብራውያን አቆጣጠር በሦስተኛው ወር በግብጻውያንም አቆጣጠር በአሥረኛው ወር ይስሐቅ በነገሠ በአሥረኛው ዓመት ጽዮን በተባለ በሰኔ ወር በሃያ ሰባተኛው ቀን በሃያ ሠርቀ ሌሊት ከሐምሌ መግባት ዘጠኝ ቀን አስቀድሞ በሰኔ ወር በሃያ አንደኛው ቀን ነው።የወሩም ስም በሮሜ ወሮች ከዕብራውያን ወር ጋር በመባቻ አንድ የሆነ ዮልዮን ነው። በዐሥራ ስምንት አበቅቴ በሰባት ጥንተ ዮን በሦስት እንድክትዮን በስድስት ጳጉሜን በሁለት ቀን ዐውደ ዕለት በወንጌላዊ ዮሐንስ ዘመን በሰግላ ሀገር ሳለን በረቡዕ ቀን ከቀኑ በዘጠኝ ሰዓት ነው

ሥላሴን ስለማመንን ዳግመኛም ስለ እግዚአብሔር ልጅ ሰው እንደሆነ የሚናገር የምሥጢር መጽሐፍ ደረሰ ተፈጸመ ለእርሱ ምስጋናና ውዳሴ ይገባል ለዘላለሙ አሜን፡ አሜን።

.......... /// ..............